# አገር እንዴት ሰነበተች  ቁጥር 12

መጋቢት 25ቀን 2014ዓም (03-04-2022)

ያገራችን የሳምንቱ ሁኔታዋ ካለፈው በባሰ ደረጃ ያሽቆለቆለበት፣በመከራ ላይ መከራ፣በችግር ላይ ችግር የተፈራረቀበት እንጂ የተሻለ አይደለም።ችግርና ተስፋ ቢስነቱ የሕዝቡን ምሬት አደባባይ አውጥቶታል። በኑሮ ውድነቱ፣በሥራ ማጣቱ፣ሰላምና ፍትሕ አልባነቱ ፣ሕዝብ ከሚችለው በላይ ሆኖበት ብሶቱን ያንጸባረቀበት ሳምንት ነው።

ካለፈው እሑድ ስንነሳ በአማራው ክልል በአማራው የተማሪዎች ማህበርና  በአማራው ወጣቶች ማህበር ቅንጅት የተጠራው ሕዝባዊ ተቃውሞ እንደተጠበቀው ሳይሆን በደብረማርቆስ፣በባሕርዳር፣ በደብረብርሃን፣በላስታና ላሊበላ፣በቆቦእንዲሁም በትናንሽ ከተማዎች ለተወሰነ ሰዓት ሰልፍ ተካሂዶ ነበር።ከሁሉም ቦታ ከተደረጉት ሰልፎች የቆቦው ብዙ ሕዝብ የተሳተፈበትና ጠንከር ያለም መፈክርና የተቃውሞ ድምጽ የተሰማበት ነበር።የሕዝባዊ ሰልፉ ጥሪ የሚጠበቀውን ያህል መልስ ያላገኘው በመንግሥት በተለይም በአማራው ክልል መሪዎች በኩል የተደረገው የመከላከል እርምጃ፣ዛቻና የፖሊስ ሃይል ማሰማራትን ጨምሮ ከፍተኛ ዝግጅት በመደረጉ ሕዝቡ በፍርሃት ላለመሳተፍ ተገዷል።ደፍረው በወጡትም ላይ በድብደባ ጉዳት የደረሰባቸው ሲሆን  አዘጋጆቹም በፖሊስ ተወስደው ለአጭር ሰዓታት ታስረው በሕዝቡ ጫጫታ በማስጠንቀቂያ ለመለቀቅ ችለዋል።

የሕዝብ ተቃውሞ በአብዛኛው አምባገነናዊ  መንግሥታት በኩል በሰላም እንደማይስተናገድ የታወቀ ነው።እንደመንግሥቱ ጸባይና አቋም ለተቃውሞ ሰልፍ የሚሰጠው ምላሽ የተለያዬ ነው።በዴሞክራሲ አገሮች የሚደረገው ሕዝባዊ ተቃውሞ በአግባቡ የሚስተናገድ ሲሆን ተጠያቂው አካል ወይም መንግሥት ለጥያቄው መልስ የመስጠት ግዴታ አለበት።አልፎ አልፎም የፖለቲካ ድርጅቶች የተቃውሞው መሪ ወይም አካል በመሆን ይሳተፋሉ።መንግሥት ለሰላማዊ ሰልፍ በወጣው ሕዝብ ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ወይም በሕዝቡ ተቃውሞ ጀርባ ሌላ ፍላጎት ያለው አፍራሽ አካል ወይም በጥባጭ ቡድን እንዳይጠቀምበት የፖሊስ ጥበቃ ይመድባል።ፖሊስ ስነስርዓት ከማስጠበቅ የተለዬ በሰልፈኛው ላይ ዱላ አይሰነዝርም።

እንደ ኢትዮጵያ ባሉ አገሮች ውስጥ ብዙውን ጊዜ ሥልጣን የሚያዘው በጉልበትና በሴራ ስለሆነ ለዴሞክራሲ ጥያቄ አለርጂክስ፣ ባዕድና ጠላቶች ናቸው።ሕዝብን አያከብሩም፣ለጥያቄውም መልስ አይሰጡም።እሩጠው የሚሄዱት የበቀል ዱላ ለመምዘዝና ሕዝቡን ሰጥ ለጥ አድርገው ለመግዛት ወደሚችሉበት የሃይል አጠቃቀም ነው።ለዚያም ነው በብዙ አገራት ሕዝቡ አደባባይ ወጥቶ ጥያቄ ከማቅረብ ይልቅ ነፍጥ መዞ ለመፋለም የሚገደደው።ላለፉት ግማሽ ክፍለዘመን የኢትዮጵያ ሕዝብ ለመብቱ በብዙ መንገድ ሲታገል ኖሯል።ግን ለጥያቄው ተገቢ  መልስ አላገኘም።አሁንም በመጠዬቅ ላይ ነው።ጭራሽ በከፋ የኑሮ ክብደት ውስጥ የተዘፈቀው ሕዝብ ሰሚ ካላገኘ፣ለጥያቄውም መልስ ካልተሰጠው፣ከሚማቅቅበት የኑሮ አዘቅት ለመውጣት የሚችልበት ብልሃት ካላገኘ የአደባባይ ተቃውሞውን ወደ አመጽ ለመለውጥ የሚገደድበት የመጨረሻ ደረጃ ላይ መድረሱ የታዬበት ሳምንት ነው።ባለፈው ዝግጅታችን ሁሉም ያለቅሳል ማለታችን የሚታወስ ነው።አዎ ሁሉም ያለቅሳል። የመንግሥት ቅጥረኛውም ሳይቀር ያለቅሳል።

በሰሞኑ በኦሮሞ ክልል የሚኖሩ የመንግሥት ተቀጣሪዎችና የግል ተዳዳሪዎች በደም ፍላት ያሰሙት እሮሮ ሁኔታው ወደዬት ሊያመራ እንደሚችል አመላካች ነው።አንዱ የመንግሥት ተቀጣሪ አንድ ክፍል

ያላት ቤት ኪራይ 5000 በደረሰበት አገር እኔ ባለ4000ሽህ ብር ደመወዝተኛ እንዴት አድርጌ ልኖር እችላለሁ ካሉ በኋላ ሌላው እዩበላ እኔ በራብ አልሞትም፣ አጠገቤ ያለውን የሚበላውን ባለሃብት ዘርፌ እበላለሁ በማለት ለከበርቴዎችና ለመንግሥት ባለሥልጣናት የነገውን ክስተት ሳይፈሩ ገልጸዋል። አክለውም ሃብታሙ ካለ ድሃው ሊኖር አይችልም፤ደሃው ከሌለ እናንተም አትኖሩም፣ጥጋባችሁን በልኩ አድርጉት ሲሉ መክረዋል።ሌላዋ እናት ደግሞ የማገኘው 1414ብር፣አንድ ሊትር ዘይት 1200 በሆነበት አገር እንዴት ነው ልኖር የምችለው ሲሉ እሳቸውና ቤተሰባቸው ከአንድ ሊትር ዘይት የረከሱ መሆናቸውን በንዴት ገልጸዋል።ሌላው የሚያሳዝነው ደግሞ የእኚህ እናት ደመወዝ 3000 ብር ሆኖ ሳለ ከሳቸው በላይ 1500 ብሩን እዩነጠቀ የሚወስደው ሥራውን ያስቀጠራቸው ደላላው ወይም ኤጀንሲ መሆኑ ነው። እንደ ኢትዮጵያ ባለ አገር ውስጥ አሠሪና ሠራተኛ በቀጥታ ሊገናኝ በሚችልበት ሁኔታ እያለ፣ከለለም መፍጠር ሲቻል በባለሥልጣኖች መረብ የተተበተበ ኤጀንሲ የተባለ የሌባ ቡድን በተቋም መልክ ጣልቃ ገብቶ የድሆቹን የድካም ዋጋ ሲዘርፍ መስማት የወንጀሉን መስፋፋት በግልጽ ያሳያል።ለዚያም ነው አፋችንን ሞልተን ሥርዓቱ የሌቦች ሥርዓት ነው ያልነው፣የምንለውም።

የሕዝቡን ብሶትና ቁጣ የሚያሳዬው የድምጽ ቅጂ ይህን ይመስላል ተከታተሉት።

https://youtu.be/vmDwc1lvLyM

የቱን አንስተን የቱን እንደምንተወው ይከብዳል።ለኦሮሙማው መሪ ለሽመልስ አብዲሳ ጽ/ቤት መገንቢያ ይሆናል በተባለው ቦታ ላይ ይኖሩ የነበሩት ዜጎች በሦስት ቀን ውስጥ ቤታቸውን ለቀው እንዲወጡ መታዘዛቸውን ባለፈው ስርጭታችን ገልጸን ነበር።አሁን ባገኘነው መረጃ እንዲለቁ ከታዘዙት መካከል በዕድሜ ጸና ያሉ ሁለት አዛውንቶች በድንጋጤ ህይወታቸው ማለፉን ነው።ሌሎቹም ባይሞቱም በቁማቸው እንደሞቱ በምሬት ገልጸዋል።አንዲት አራስ ልጄን የት ይዤ ልግባ?በመንገድ ዳር ልውደቅ?ስትል እምባዋን እዬረጨች ብሶቷን ስትናገር፣ ታዳጊ ሕጻናትም ከምንኖርበት ስንነሳ ከምንማርበት ት/ቤትም መውጣት አለብን ማለት ነው፤ታዲያ እንዴት ነው ለታዳጊው ትውልድ ለእኛ የማያስብ መንግሥት አገር ትበልጽግ የሚለው?ማንን ይዞ ለማበልጸግ ነው? በማለት መንግሥትን በራሱ ባቀረበው ስለት ቆርጠውታል።የኦሮሙማው ተስፋፊ ቡድን በጫካ ኦነግ፣በቤተመንግሥት ብልጽግና በሚል ስም የሚፈልገውን በወረራና በትእዛዝ እያስፈጸመ ነው።በቅርቡ የኦነግ አሸባሪ ቡድን ከኦሮሚያ ልዩ ሃይል ከተባለው ጋር በመተባበር በሰሜን ምስራቅ ሸዋ ፣ምንጃር ሸንኮራ ልዩ ስሙ አውራጎዳና የተባለውን የጅቡቲ መገናኛ መስመር በመውረር የአማራውን አጽመርስት በመዳፉ ሥር ለማስገባት ያደረገው ሙከራ ባይሳካለትም በአጣዬ በኩል የሚያደርገውን ተደጋጋሚ ጥቃት ቀጥሎበታል።

በአዲስ አበባ ከተማም ሕዝብን አፈናቅሎ ቦታዎችን መንጠቁ የቀጠለ ሲሆን እብሪተኛ አሮሙማው ቡድን ታሪካዊውን የባሕልና የኪነት መስክ የሆነውን የያሬድን የሙዚቃ ትምህርት ቤት አፍርሶ የኦሮሞ ፍርድ ቤት ለመገንባት መወሰኑ ተሰምቷል።ይህ ሁሉ ድፍረት አዲስ አበባን ባለቤት የሌላት ከተማ አስመስሏታል።

ሌላው የሰሞኑ ግርምት የጫረው ክስተት በአንድ ዋንጫ ካልጠጣን ብለው ሜዳውን ያስጨነቁት ኢሳያስና አብይ በተቃርኖ ላይ መቆማቸው ነው።አብይ ከአሜሪካኖች፣ ከምዕራባውያንና እንዲሁም ከወያኔ ጋር ያደረገው መቀራረብ የፈጠረውን ልዩነት ተከትሎ የኤርትራው መሪ በአምባሳደር ደረጃ የነበረውን ግንኙነቱን በጉዳይ አስፈጻሚ ደረጃ ዝቅ አድርጎታል።ለኢትዮጵያና ለኤርትራ ሕዝብ ዘላቂ ሰላምና እድገት የሚረዳው ብቸኛ መንገድ ከአምባገነኖች መዳፍ ለሚላቀቁበት ትግል ተባብረው ሲቆሙ ብቻ ነው።የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነቱ በመሪዎች መቀራረብ ወይም መራራቅ መወሰን

የለበትም።ባለፈው የታሪክ ግንኙነታቸው ላይ አብሮነታቸውን በጥምረት ማለትም በፌዴራላዊ ግንኙነት ደረጃ ላይ ቢያደርጉት አስተማማኝ ሰላምና እድገት ላይ ይደርሳሉ።የውጭም ጠላት ሊደፍራቸው አይችልም።

ሕዝብን ከአዲስ አበባ ማፈናቀል ትናንትናና ዛሬ የተጀመረ ሳይሆን ላለፉት ሰላሳ ዓመታት በዕቅድ ሲሠራበት የኖረ ነው።ሟቹ መለስ ዜናዊ ወደፊት አዲስ አበባ ደሃ የሚኖርባት አትሆንም ማለቱ አይዘነጋም፣የአሁኑም የኦነጉ መሪ አብይ አህመድ አዲስ አበባ የተወደደበት ሰው ጥሎ ይውጣ በማለት በድፍረት ዓላማውን ለማሳዬት ሞክሯል።ይህ ሕዝብን ከአዲስ አበባ የማባረርና አዲስ አበባን የማዋጥ ፍላጎት ከሰላሳ ዓመት በፊት በኦነጉ መሪ በዲማ ነገዎ ማንሃይም በተባለ የጀርመን ከተማ በተደረገ ስብሰባ ላይ የተናገረው ነው።ፊንፊኔ የኦሮሞ ከተማ ነች፤ኦሮሞ ያልሆነው ሕዝብ መውጫ በር ተከፍቶለት ወደ የመጣበት እንዲሄድ ይደረጋል።ለኦሮሚያ የሚጠቅመው ብቻ መኖሪያ ፈቃዱን እያሳደሰ ይኖራል ብሎ ነበር።አሁን እዬሆነ ያለው ይህ ነው።ይህንን የተናገረው ዲማ ነገዎ አሁን የአብይ አህመድ አማካሪና የብሔራዊ ም/ቤት አባል ነው።ሕዝቡ በአንድነት ታግሎ ካላስቆመው የከፋው ይመጣል።በቤት ኪራይ፣በግብር፣በኑሮ ውድነት ማበሳጨቱም ለዚያ ዓላማ መዳረሻ ስልት ነው።

ሰሞኑን የከተማዎችን የኑሮ ውድነት የሚከታተል ዓለም አቀፍ ተቋም ባወጣው መግለጫ አዲስ አበባ ከ15 የአፍሪካ ለኑሮ ከባድ ከሆኑት ውድ ከተማዎች በአንደኛ ደረጃ መቀመጧን አረጋግጧል።በዚህ የመመዘኛ ሰንጠረዥ ለአዲስ አበባ የተሰጣት የደረጃ መለኪያ 58.9 ነው።ሌሎቹም በተከታይ ደረጃ ተሰልፈዋል።ይህ ወዴት ያመራል?ወደለዬለት ቀውስና ብጥብጥ ብሎም ደም መፋሰስና እልቂት እንደሚያመራ አያጠራጥርም። ከ60% በላይ ሥራ አጥ በሆነባት ከተማ የኑሮ ውድነት ሲጨመርበት ከሚመጣው ይሰውረን ያሰኛል።የራበው ሕዝብ መሪዎቹን ይበላል የሚባለው ከመሪዎችም አልፎ ሕዝብ እርስ በራሱ እንዳይባላ መላና ዘዴ ሊፈለግለት ይገባል።የተሻለው ዘዴ ደግሞ ለዚህ ምስቅልቅል ኑሮና አለመረጋጋት የዳረጋትን የጎሳ ፖለቲካና ድርጅቶቹን ከነአመለካከታቸው ማሶገድ ነው።አዲስ አበባን የአዲስ አበቤዎች ብሎም የኢትዮጵያውያን ከተማ መሆኗን ማረጋገጥ ነው።በርሃብና በጎሰኞች እጅ በቆንጨራ ከመሞት ለነጻነትና ለመብት መሞት ትልቅ ዋጋና ክብር አለው።አረመኔዎችን ታግሎ በመጣል በትንሽ መስዋእትነት ብዙ ህይወት ማትረፍ ይቻላል።

በዚችው ድህነት በወረራት ከተማ ውስጥ ነው ለሕንጻ ግንባታና ማደሻ በቢሊዮን የሚቆጠር ብር የሚፈሰው።በዚችው በሚሊዮን የሚቆጠር ድሓ ሕዝብ በሚተራመስባት ከተማ ውስጥ ነው ጥቂቶች ሥልጣንና ሃብታቸውን ተመክተው አስረሽ ምችው ኑሮ የሚኖሩባት፣በአውሮፓ ከተሞች የማይነዱ ውድ መኪናዎች የሚያሽከረክሩባት። ኧረ የግፍ፣የጭካኔውና የራስ ወዳድነቱ ድንበሩን አጣ!የማን ያለህ ይባል?የፖለቲካ ድርጅት ነን የሚሉትም በሌሎቹ ላይ የሚያዩትን ቅንጡ ኑሮ ለመኖር ወይም ተካፋይ ለመሆን እንጂ ለሕዝቡ የቆሙ አልሆኑም።ጥቂት በመንቀሳቀስ የሕዝቡን ብሶት የሚከታተለው ባልደራስ የተባለው ድርጅት ነው። እሱም ቢሆን ችግሩ በአንድ ድርጅት የሚፈታ ካለመሆኑ አንጻር ያገሪቱን ጠቅላላ ችግር ይፈታል ተብሎ አይጠበቅም።ውስብስብና ብዙ ከመሆኑ አንጻር የሌሎቹንም ተሳትፎ ይጠይቃል።ለዚያም ነው ከሁሉም የተውጣጣ የሽግግር መንግሥት ይመሥረት የምንለው።ይህ ብቻ ነው አገራችን ከገባችበት ማጥ፣ሕዝባችን ከሚገፋው አስከፊ ኑሮና ስጋት ሊወጣ የሚችልበት ብቸኛው መንገድ።

የአብይ አህመድ የሚወክለው የኦነግ መራሹ መንግሥት ከአሜሪካኖቹ የቅጣት አለንጋ የሚወጣ መስሎት ለወያኔ ማጎብደዱን በግልጽ ያዬንበት ፣እርዳታ ያለምንም ገደብና ፍተሻ ወደ ትግራይ እንዲገባ የፈቀደበት ሳምንት ነው።በዚህ ብቻም አላቆመም የወልቃይትና የራያ ለም መሬት በወራሪው በወያኔ ፍላጎትና ጥያቄ መሠረት እንዲፈታ የሚል ውሳኔም በተላላኪዎቹ በደመቀ መኮንንና በአገኘሁ ተሻገር

በኩል አስተላልፏል።ይህ በሕገመንግሥቱ መሰረት  በሕዝበ ውሳኔ ይጠናቀቃል  በሚል ሽፋን የሚደመደም ሕገወጥ ቅሚያን ሕጋዊ ለማድረግ የታሰበና  ወያኔ ለዓመታት ሲጠይቀው የነበረ ነው። የመሬቱ ታሪካዊ ባለቤት የሆነው አማራው ከይዞታው በጉልበት ተነጥቆ መኖሩ እዬታወቀ ያንኑ ለነጣቂው ለወያኔ አሳልፎ መስጠት አነግና ወያኔ በአማራው ላይ ካላቸው ተመሳሳይ የጠላትነት አቋም በመነሳት መሆኑን ለማወቅ ነብይ መሆን አይጠይቅም።ገጦና ፈጦ የሚታይ ሃቅ ነው።

የወያኔም በጉልበት ቦታዎቹን ለመያዝ የሚያደርገው ጦርነት፣ከያዛቸውም ቦታዎች ያለመልቀቅ ፍላጎት ለሕዝበ ውሳኔው አንደ አስገዳጅ  መሳሪያ አድርጎ ለመጠቀም  ይረዳኛል ከሚል ስልታዊ ሃሳብ የመነጨ ነው።የአብይ አህመድ መንግሥት ከአሜሪካኖቹ ዱላ አመልጣለሁ ሲል ሌላ ዱላ ተመዞበታል።በሕዝብ ተወካዮች  በኮንግሬሱ ኮሚቴ በኩል የረቀቀው HR6600 የተባለው የእቀባ አንቀጽ በመንገድ ላይ እያለ ሌላ S3199 የተባለ አንቀጽ በተጨማሪ  በኮንግሬሱ ኮሚቴ በኩል ለመላው የኮንግሬስ አባላት ተላልፎ ከጸደቀ በኋላ በፕሬዚዳንቱ ፊርማ እንዲጸድቅና ተግባራዊ እንዲሆን የማድረጉ እንቅስቃሴ ከመጨረሻው ጠርዝ ላይ ደርሷል።የኦሕዴድ /አነጉ መራሹ ብልጽግና የሚይዝ የሚጨብጠውን አጥቶ ደጋፊዎቹን ለተቃውሞ እንዲወጡለት ተማጽኗል።ምንም እንኳን አንቀጾቹ  የወያኔን መሪዎችንም የሚመለከት ቢሆንም የአንቀጹ መርቀቅና ከዚህ ደረጃ ላይ መድረሱ  በወያኔ ጎራ ደስታ በአብይ አህመድ ጎራ መርዶ ሆኗል።

የአሜሪካኖቹ እንቅስቃሴ እውነት ለኢትዮጵያ የሚረዳ ነው ለማለት ካላቸውና እስካሁን ከሚከተሉት ፖሊሲያቸው አንጻር ባንደፍርም  በሰብአዊ መብት ጥሰት የተጠረጠሩ ሰዎች የትም ይሁን ዬት ለፍርድ ቢቀርቡና ተጠያቂ ቢሆኑ ደስ ይለናል እንጂ አይከፋንም።አገራችን የራሷን ችግር በራሷ፣ወንጀለኞችንም የሚመለከተው ጉዳይ በራሷ ሕግና የፍትሕ ተቋም ብትፈታው የተሻለ ነው።በአጠቃላይ ግን ከአሜሪካኖችም ሆነ ከአጠቃላዩ የምዕራቡ ጎራ ከራሳቸው ጥቅም በላይ  ለኢትዮጵያ ጥቅም ይቆማሉ ብሎ ማሰብ ሞኝነት ነው።በሰብአዊ መብት ማስከበርና በዴሞክራሲ ማስፈን ሽፋን ሌሎች አገሮችን ሲያወድሙና ንጹሃንን ሲጨፈጭፉ፣ከአምባገነን መንግሥታትም ጎን ሲቆሙ ባዬንበት ዓይናችንና በሰማንበት  ጆሯችን ይህ እንቅስቃሴያቸው ለበጎ ነው ብለን ለመውሰድ ይከብደናል። በሰብአዊ መብት ጥሰት መጠዬቅ ቢኖር ኖሮ እነሱ የመጀመሪያዎች ይሆኑ ነበር።ለስሙ ባቋቋሙት የዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ተፈርዶባቸው እስር ቤት የሚገቡት የአገልግሎት ዘመናቸውን ጨርሰው፣ሕዝብ አንቅሮ የተፋቸውን መሪዎችና ወንጀለኞችን በማሰር ነው።በነሱም ፈንታ በዴሞክራሲና በለውጥ ስም ሌላ ፈረስ ተክተው መጋለባቸው የተለመደ ነው።አሁንም የወያኔም ሆነ የብልጽግና መራሹ ቡድን ቢወገድ ሌላ ተላላኪ መንግሥት ከማቋቋም አይመለሱም።የኢትዮጵያ ሕዝብ ከተደጋጋሚ መከራ፣ከምጣድ ላይ ወደ ሌላ ምጣድ ከመወርወሩ በፊት ለባዕዳን አጎብዳጅና ተገዢ ያልሆነ ፍጹም አገር ወዳድ የሆነ መንግሥት ለማቋቋም ተባብሮ ከመታገል የተሻለ ምርጫ የለውም።

በአጠቃላይ የአገራችን ሁኔታ ሲታይ ለውጥ ሊወለድ በዘጠነኛው ወር ላይ የደረሰ ጽንስ ይመስላል። የሚወለደው ልጅ ግን ከፉና መናጢ እንዳይሆን እንደሚመኙ ወላጆች ለውጡም  ለባሰ ሥርዓት እንዳይዳርገን የሕዝቡና የእኛም ምኞት ነው።የኦሮሙማው ጎራ ውስጥ ያሉት በስም እንጂ በአቋም እንደማይለያዩ በበቂ ማስረጃ የምናውቀው ነው።ከሰሞኑም የኦፌኮ መሪ የሆነው መረራ ጉዲና  ኦነግ በኦሮሞ ክልልና ከዚያም ውጭ በአማራውና በሌላው ሕዝብ ላይ የሚፈጽመውን ጭፍጨፋ በተመለከተ ምንም ቃል ሳይተነፍስና አድራጎቱንም ሳያወግዝ ቀይቶ  በምክር ቤቱ አሸባሪ ተብለው የተወገዙት ኦነግ (ሸኔ)ና ወያኔ ካለምንም ቅድመ ሁኔታ ለብሔራዊ ምክክሩ ተሳታፊ መሆን አለባቸው የሚል ሃሳብ ሰንዝሯል።የሚያስገርም አይደለም፤ ከአሜሪካ ተሸክሞት የገባው የኮንፍድራሊስቶቹ ቡድን የጋራ አቋም ነው።የወያኔ ቤተሰቦች መሆናቸውን ያሳዬበት መንገድ ነው።እኛም በእንግሊዝኛው “Birds

Of The Same Feather Flock Together" በአማርኛችንም ግም ለግም አብረህ አዝግም ብለን አልፈነዋል።

የኦሕዴዱ መሪ አብይ አህመድ በሕዝቡ ኑሮ ላይ መቀለዱንና መሳለቁን ቀጥሎበታል።ከሳምንት በፊት በቅጠል ላይ ጨው ነስንሳችሁ ብሉ።ዘወትር እንጀራ በወጥ መብላት አይቻልም ያለው ከጆሯችን ሳይርቅ አሁን ሰሞኑን ደግሞ ዳቦ በሙዝ ወይም በማንጎ ተመገቡ ሲል በሕዝብ ችግር ላይ አሹፏል።ዳቦ በሌለበት፣ቢኖርም አንዷ ስስ ዳቦ ከ4 ብር በላይ በምትሸጥበት ፣በድርቅ ምክንያት ቅጠል፣ሙዝና ፓፓዮ ቀርቶ ሳር በማይበቅልበት አገር በሚኖረው ሕዝብ ላይ በዚህ መልኩ ማላገጡ ይበልጥ ማንነቱን አጋልጧል። ከአምስት ዓመት በፊት ከአንድ ሺህ ብር በላይ የማያወጣው አንድ ጆንያ ምስር የሁዳዴ ጦምን በማሳበብ አሁን 10,000ሺህ ብር ማለትም አንድ ኪሎ ምስር 100 ብር ሲሸጥ የዋጋ ቁጥጥር ለማድረግ የደፈረ የመንግሥት አካል የለም።በአህያ ጭኖ የሚሸጠው የከባቢው ኦሮሞ ስለሆነ ያባትህ ቤት ሲዘረፍ አብረህ ዝረፍ በሚል ህሳቤ ያሻውን እንዲያደርግ የተፈቀደለት ይመስላል።ተረኝነቱ መረን የለቀቀ ለመሆኑ ከዚህ የበለጠ ማሳያ የለም።ሌላ ሌላውም እንደዚሁ!

ሌላው የጉድ አገር የሚያሰኘው ድርጊት ከሙቶ ሃምሳ ዓመት በፊት በዳግማዊ አጼ ምኒሊክ ከፈረንሳይ የተገዛ የጦር መሣሪያ(ጠብመንጃ)ከተቀመጠበት ከቤተመንግሥት ግምጃ ቤት ተሰርቆ በውጭ አገር ገበያ በተለይም በአሜሪካ በጣም ውድ በሆነ ዋጋ መሸጡን የሚያመለክት የቪድዮ ማስረጃ ይፋ መውጣቱ ነው። በቤተመንግሥት ውስጥ ያሉትን ብቻ ሳይሆን ቢቻላቸው ቤተመንግሥቱንም አውጥቶ ከመሸጥ የሚመለሱ ሌቦች አይደሉም።አገርን መግደል ማለት ታሪክና ቅርስን ማውደምና ማጥፋት ነው።ይህንንም በስፋት ተያይዘውታል።

ሁሉም በያቅጣጫው ጩኸቱን ተያይዞታል በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል የሚሠሩት ሃኪሞችና የጤና ባለሙያዎች ብሶታቸውን አደባባይ ወጥተው አሰምተዋል።የሙስሊም ኦርቶዶክሳውያንም ጎራ ለይተው እርስ በርሳቸው ተደባድበዋል።በተማሪዎች መካከል የተፈጠረው ይህ የሙስሊሞች ተቃውሞና የእርስ በርስ ግጭት ወዴት ሊያመራ እንደሚችል ባይታወቅም በቀላሉ የሚበርድ አይመስልም።በላኢላ ሃይለላና አላህ አክበር እንዲሁም ጁንታው ይሻላል የሚሉ መፈክሮችን ያስተጋባው ይህ ግብግብ ለባዕዳን በተለይም ለግብጾች ሴራ መግቢያ ቀዳዳ እንዳይሆን መጠንቀቅ ያስፈልጋል።የሙስሊም ወገኖቻችን አግባብ ያለው ጥያቄም ከሆነ መልስ ሊሰጣቸው ይገባል።ጎራ ለይቶ እርስ በርስ መጋጨቱና በጠላትነት መቆሙ ግን ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል፤ለተረኛው ኦሮሙማ ቡድንም አገር ለማፍረሱ ዓላማ አጋዥ ጉልበት ይሆናል።በጎሳው ንትርክ ላይ የሃይማኖት ንትርክ ሲጨመርበት ያገራችንን ሕልውና በቅጡ ይጎዳል፣ለአደጋም ያጋልጣል።በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ያደርገዋል።ስለሆነም ሁሉም ጉዳተኛ በአንድ ጣራ ሥር ተሰባስቦ ለችግሩ መፍትሔ ከመፈለግ የተሻለ አማራጭ አይኖርም።ስለሆነም አሁንም ደግመን ደጋግን ብሔራዊ አስተባባሪ ኮሚቴ ይፈጠር እንላለን።በዚህም መልክ የተቀናጀ ሕዝባዊ ትግል ለድል ይበቃል።

የአምባገነኖች ሥልጣንና የሚፈጽሙት ግፍ ለዘለዓለሙ ቋሚ ሆኖ አይኖርም።ያንን የሚያሰግድ ለውጥ ምንም እንኳን ጊዜው ቢረዝምም ጊዜውን ጠብቆ ይመጣል። ለውጥ አይቀሬ ነው! በማንም ፍላጎት ሊቀር ወይም ሊታገድ የማይችል የተፈጥሮ ሕግ ነው።

ይህንን እውነታ የሚገልጽ ሳም ኩክ የተባለ ጥቁር አሜሪካዊ ከስልሳ ዓመት በፊት በሙዚቃ የተነበዬውን ለማቅረብ እንወዳለን።

ሳም ኩክ በጃንዋሪ 22 ቀን 1931 በሚሲሲፒ ከተማ ተወልዶ በዲሴምበር 11ቀን 1964 በተወለደ በ33 ዓመቱ በሎስአንጅለስ ከተማ በሰው እጅ ተገሎ ህይወቱ ያለፈ ታዋቂ ሙዚቀኛ ፣ዘፋኝና ገጣሚ ነበር።

እሱም እንደሌሎቹ ጥቁሮች በነጮች የዘረኝነት አለንጋ ተገርፎ ያደገና የቋጠረውን ብሶትና ብስጭት በሙዚቃው ሲገልጽ የኖረ ነበር።ከተጫወታቸው የብሉስና ሶል ጨዋታዎች ውስጥ “ለእኔ መውደድ በምላሹ ብትወጂኝ /ብትወደኝ ወይም  ፍቅርና መዋደድ ቢኖር ዓለማችን ድንቅ ዓለም ትሆን  ነበር” “What a wonderful world that would be” የሚለው ይገኝበታል።ከሁሉም ዘፈኖቹ ይበልጥ ተስፋና ምኞቱን የገለጸበት  ጥቁሮች የሚገፉበት፣ የነጮች የበላይነት የሰፈነበት የዘረኞች ሥርዓት እንደሚቀዬር ያንጎራጎረው “A change is gonna come!” በማለት የለውጥን አይቀሬነት የገለጸበት ዘፈኑ ነበር።እስከአሁንም ለውጥ እንዲመጣ ለሚፈልጉ ሰዎች የተስፋ ስንቅ ሆኖ  ያገለግላል።

ተወዳጁ ዘፈን ይህንን ይመስላል፣

https://youtu.be/wEBlaMOmKV4

ወደ ዘፈኑ የግጥም ስንኞች  ስናመራራ የሚከተሉት ናቸው።

የዘፈኑ እርእስ

A Change is gonna come

I was born by the river in a little Tent

And just like the river, I have been running ever since

It’s been a long, a long time coming

But I know a change gonna come!

Oh, yes It will!

It is too hard living,but I am afraid to die

Because I don’t know what’s up there beyond the sky

It’s been a long, a long time coming

But I know a change gonna come

Oh,yes it will!

I go to the movie,and I got down town

Somebody keep telling me don’t hang around

It’s been a long, a long time coming

But I know a change gonna come

Oh,yes it will!

Then I go to my brother and I say brother help me please!

But he winds up,knockin'me back down on my knees.

Oh,There been times that I,thought I couldn't last for long

But now I think I am able to carry on.

It's been a long, a long time coming

But I know a change gonna come

Oh, yes it will!

I see it now and I said a chang is gonna coming right now.

የአማርኛ ትርጉሙ ይህንን ይመስላል

ለውጥ አይቀርም! ይመጣል!

በወንዝ ዳር ላይ ባለች ትንሽ ድንኳን(ጎጆ) ውስጥ ተወልጄ፣ከዚያን እለት ጀምሮ እንደ ወንዙ ሳላርፍ፣(ስንከራተት) እኖራለሁ፤ ግን እረጅም ጊዜ ቢወስድም ለውጥ እንደሚመጣ አውቃለሁ።አዎ! በእርግጥም ለውጥ ይመጣል።ኑሮ ከባድና አስቸጋሪ ቢሆንም መሞትን እፈራለሁ፣ምክንያቱም ከሞት በኋላ ከሰማያት ሰማያት ጀርባ ምን እንደሚጠብቀኝ አላውቅምና ነው።ሆኖም ግን ብዙ እረጅም ጊዜ ቢወስድም አሁንም ለውጥ እንደሚመጣ አምናለሁ።

ከእለታት አንድ ቀን ሲኒማ ለማዬት ወደ ከተማ ብሄድ አንዱ ያገኘሁት ሰው ሁለተኛ ብቅ እንዳትል!ብሎ ደጋግሞ አስጠነቀቀኝ፤እኔም ምንም እንኳን ረጅም ጊዜ ቢወስድም ለውጥ እንደሚመጣ አውቃለሁ።እርግጠኛ ነኝ ለውጥ ይመጣል።

ቢጨንቀኝ ወደ ወንድሜ ሄድኩና ወንድሜ እባክህ እርዳኝ ብለው ጀርባውን ሰጠኝ፤ ፊት ነስቶ መለሰኝ፤የመኖር ተስፋ የቆረጥኩበት ጊዜ ነበር።አሁን ግን ተስፋ ሳልቆርጥ ሁሉንም ችዬ እንደማልፈው ተረዳሁ፤ረጅም ጊዜ ቢወስድም ለውጥ እንደሚመጣ አውቃለሁ።አዎ! ለውጥ ይመጣል፣አሁን ይታዬኛል ለውጥ ይመጣል፤ በእርግጥም ለውጥ ይመጣል እላለሁ።

አዎ ለውጥ ይመጣል!

ሌላው በዚያው ወቅት በነበረው የዘረኞች ሥርዓት በጥቁሮች ላይ የሚያደሰውን ጭቆና ተቃውሞ ስለ ለውጥ ትንቢት የተናገረውና ለለውጥ ጥያቄ ሚሊዮኖችን በአደባባይ ለማውጣት የቻለው ማርቲን ሉተር ኪንግ ነበር ። ሕልም አለኝ፣ይታዬኛል "I Have A Dream" የሚለው ንግግሩ እንደትንቢተኛ አስቆጥሮታል።በዚህ ታሪካዊ ንግግሩ ውስጥ የነጭና የጥቁር ልዩነት ሳይኖር ልጆች እጅ ለእጅ ተያይዘው ይጫወታሉ፣ያድጋሉ፣በአንድ ትምህርት ቤት ይማራሉ...ወዘተ የሚል ተስፋ የሰነቀ ንግግር ነበር።ምንም እንኳን ሙሉ ለሙሉ እኩልነት ሰፍኗል ባይባልም፣ጥቁሮች አሁንም በዘረኛ ነጭ ፖሊሶች ጥይት የሚገደሉም ቢሆን አንጻራዊ መሻሻል መምጣቱ አይካድም።ለዘለቄታ እኩልነት ግን አሁንም ትግሉ በየፈርጁ ቀጥሏል።የ "BLACK LIVES MATTER"እንቅስቃሴ የዚያ ማስረጃ ነው።በአገራችንም ጥያቄ ዙሪያ "NO MORE"የሚለው እንቅስቃሴ ፈሩን ባይለቅና ቢቀጠልበት ኖሮ ከአገራችን አልፎ

ለዓለም ጭቁን ሕዝቦች ትግል ማቀጣጠያ ነዳጅ ይሆን ነበር።ብዙዎችም በአፍሪካ፣በእስያ፣በሰሜንና በደቡብ አሜሪካ ተቀብለው ማስተጋባት ጀምረው ነበር።የመፈክሩ ጠንሳሽ በሆነችው በሔርሜላ አረጋዊ በኩል በመዳከሙና በነአብይ አህመድ በመጠለፉ ምክንያት ንቅናቄው ሊቀጥል አልቻለም። ሆነም ቀረም ግን ግፍና መከራ እስካለና  የለውጥ ሃይል እስካለ ድረስ ለውጥ አይቀርም።አገራችን ላይ የሰፈነው የጎሰኞች ሥርዓትም ምንም ያህል ከባድና አስቸጋሪ፣የሚከፈለውም ዋጋ ብዙና ከፍተኛ ቢሆንም እንደሚወገድ እርግጠኞች ነን። እኛም እንደ ሳም ኩክስ ለውጥ አይቀርም እንላለን።እኛም እንደ ማርቲን ሉተር ኪንግ  የጎሳና የእምነት ልዩነት ሳያሸንፈንና ሳያንበረክከን በአንድ ላይ እጅ ለእጅ ተያይዘን ይህንን ክፉ ቀን እናልፋለን፣አገራችንንም ኢትዮጵያን ጠብቀን ለተተኪው ትውልድ እናስረክባለን የሚለው ቃላችን ከትንቢት ነት ወደ እውንነት ይለወጥ ዘንድ የበኩላችንን ለማበርከት ተነስተናል።ሁሉም ይነሳ፣ለብቻ መጮህና ማልቀስ መፍትሔ አይሆንም እንላለን።የሳም ኩክስንና የማርቲን ሉተር ኪንግንም ነፍስ ይማር!ለእኩልነት፣ለዴሞክራሲና ለፍትሕ፣ለአገር አንድነት ሲሉ የተሰዉ ጀግኖች ኢትዮጵያውያንንም ነፍስ ይማር!

የአገራችንን አንድነት፣ የሕዝባችንን ደህንነትና ሰላም ያቅርብልን!ጎሰኝነትንና ጎሰኞችን ያሶግድልን!!እኛም ለዚያ ተባብረን እንነሳ!!!

ኢትዮጵያ በነጻነትና በአንድነት ለዘለዓለም ትኑር!!